Consumer Affairs Victoria

# በህጋዊ የተዋሃዱ ማሕበራት- ለአዲስ ህጎች ስለመላመድ

ህዳር/ November 1 ቀን 2012 ዓ.ም የህጋዊ ማሕበር አንቀጽ ህግ/*Act 1981* በህጋዊ የማሕበር ማሻሻያ አንቀጽ ህግ/ *Reform Act 2012* ይቀየራል፡፡ በአዱስ አንቀጽ ህግ የሚካተተው 'የመሸጋገሪያ ቅንጅት' ሲሆን ይህም ማሕበራቱ አዲሱን ህጎች እንዲያስተካክሉ ለመርዳት ነው፡፡ እነዚህም ከዚህ በታች ተገልጸዋል፡፡

## በህጋዊ ለተዋሃደ ማሕበር ሥልጣን

በድሮ አንቀጽ ህግ መሰረት ህጋዊነት ያገኘ ማንኛውም ማሕበር በአዲሱ አንቀጽ ህግ መሰረት በህጋዊነት ይቀጥላል፡፡ ህጋዊ ውህደት ያገኘበት ቀን ችግር እንደማይኖረውና የህጋዊ ውህደት ምስክር ወረቀት ዋጋ ቀጣይነት ይኖረዋል፡፡

### የአላማው ጽሁፋዊ መግለጫ

አዲሱ አንቀጽ ህግ ሲጀምር በህጋዊ ማሕበራት የወጡ አላማዎች ጽሁፋዊ መግለጫ በቀጥታ እንደ የህገ ደንቡ ክፍል ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

አዲሱ አንቀጽ ህግ ከጀመረ በኋላ በህጋዊ መንገድ ለመጀመሪያ ጊዜ ማሕበር መሆን ለሚፈልጉ፤ ታዲያ 'ለአላማ ጽሁፋዊ መግለጫ' ለየት ያለ ቅጽ መሙላት የለበትም፤ ነገር ግን የማሕበሩን አላማ በታቀዱት ደንቦች መሰረት መስተካከል አለበት፡፡

አዲሱ የህግ መተዳደሪያ ከጀመረ በኋላ ማሕበሩ ያሉትን ደንቦች ለመቀየር ካመለከተ ታዲያ በታቀደው አዲስ ደንቦች ውስጥ የማሕበሩ አላማ ካተት አለበት፡፡

## ደንቦች

በአዲስ አንቀጽ ህግ መርሀ ግብር/Schedule 1 የሚካተት የማሕበሩ ደንቦች ማቅረብ አለበት፡፡ እነዚህም:

- የማሕበሩ ስምና አላማዎች
- የአባላት መብቶችና ግዲታዎች
- አባል ለመሆን ሲመዘገቡ ወይም ከአባልነት ሲወጡ የአሰራር ሂደት
- ቀጠሮ ለማቀናጀትና ከማሕበር ጸሀፊነት ለማቆም አሰራር ሂደት
- በአጠቃላይ ስብሰባዎችና በኮሚቴ ስብሰባዎች ላይ አጀንዳዎች እንዲያዙ ዝግጅት ስለማድረግ
- በአጠቃላይ ስብሰባዎች ላይ የቀረቡትን አጀንዳዎች ለአባላት ማቅረብ፤ ይህም ለአጠቃላይ ስብሰባ የፋይናንሻል ዝርዝር የጽሁፍ መግለጫን ያካትታል
- በአባላት በኩል ለኮሚቴ ስብሰባዎች የቀረቡትን አጀንዳዎች የማግኘት መብት (በደንቡ ውስጥ ለተጠቀሰ ማንኛውም ደንቦች)፡፡

ማሕበሩ የራሱ የሆነን ወይም የሞዴል ደንቦችን ቢጠቀምም ታዲያ እነዚህን በአዲሱ ህጎች ለመቀየር አለመጣደፍ ነው፡፡

State Government Victoria | Department of Justice

© State Government of Victoria (Consumer Affairs Victoria) 2014

## በራሳቸው ደንቦች ስለሚጠቀሙ ማሕበራት

አንድ ማሕበር **የራሱን ደንቦች** የሚጠቀም ከሆነ (የሞዴል ደንቦችን ሳይሆን) አሁን ያሉት ደንቦች እስከሚቀየሩ ድረስ ጥቅም ላይ ይውላሉ። አሁን ባሉት ደንቦች ላይ ማኛቸውም የለውጥ በአባላት ከተወሰነ በኋላ ታዲያ በመርሀ ግብር/Schedule 1 ውስጥ ላለ ለእያንዳንዱ ዝርዝር በአዲሱ ደንቦች በኩል መግለጽ አለበት። በዚህን ጊዜ በማሕበሩ ደንቦችና በአዲሱ አንቀጽ ህግ መካከል የሚጋጭ ካለ የአዲሱ አንቀጽ ህግ ተግባራዊ እንዲሆን ይፈለጋል።

## የሞዴል ደንቦችን ስለሚጠቀሙ ማሕበራት

ከነዚህ ማሕበራት አላማዎች ጋር የሚስማማ ስለመሆኑ ለመወሰን በአዲሱ ሞዴል ደንቦች ላይ ግምገማ ማካሄድ ይኖርባቸዋል። እነዚህ ማሕበራት ስላላቸው ደንቦች አዲስ ህጎች ሲጀምር በ12 ወራት ውስጥ ለቪክቶሪያ ሸማች ተጠቃሚ ጉዳይ ካላሳወቁ፤ በወቅቱ ያላቸው ደንቦች በቀጥታ በአዲሱ ሞዴል ደንቦች ይተካሉ።

አንድ ማሕበር ለቪክቶሪያ ሸማች ተጠቃሚ ጉዳይ ካላሳወቀ፣ ሊከሰት የሚችል:

- ቀደም ብሎ ወደ አዲሱ ሞዴል መቀየር
- የራስን ደንቦች መፍጠር ይሆናል።

ከህዳር/ November 1 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ ስለ አዲሱ ሞዴል ደንቦች በድረገጽconsumer.vic.gov.au/forms ላይ ያገኛሉ።

የማሕበሩ ደንቦች (የራስም ሆነ የሞዴል ደንቦች) በመርሀ ግብር/Schedule 1 ዝርዝር የተገለጹትን ማሳየት አለበት። ካላሳዩ ግን ከአዲስ የሞዴል ደንቦች ውስጥ ጠቃሚ የሆኑትን በመውሰድ በደንቦቹ ውስጥ ማስገባት ነው።

## ህዝባዊ ባለሥልጣን የሚለው በጸሀፊ ይተካል

አዲስ በወጣው አንቀጽ ህግ መሰረት ህዝባዊ ባለሥልጥን የሚለው ቃል 'ጸሀፊ' በሚል ቃል ተተክቷል።

በድሮው አንቀጽ ህግ መሰረት ማንኛውም ሰነድ በህዝባዊ ባለሥልጣን የሚታወቅ ችግር አይኖርበትም።

አንዴ አዲሱ ህግ ሲጀምር የጸሀፊ ተግባርም ሊቀጥል እንደሚች ወይም ቀደም ሲል በህዝባዊ ባለሥልጣን የተጀመረ ማንኛውም ስራ በጸሀፊው በኩል ይጠናቀቃል። ለቪክቶሪያ ሸማች ተጠቃሚ ጉዳይ ካልተነገረ በስተቀር የሚተካው ሰው ተመሳሳይ እንደሚሆን ይገመታል።

## የፋይናንሻል ጽሁፍ መግለጫ

በሶስት ደረጃ የተጠመረ አዲስ የሪፖርት አቀራረብ የአዲስ አንቀጽ ህግ ያስተዋውቃል። አንድ ማሕበር ባገኘው ገቢ መጠን የሚመደበው እንደ ደረጃ አንድ፣ ሁለት ወይም ሶስት ይሆናል። ለምሳሌ:

- ደረጃ አንድ: ከ$0 እስከ $250,000 ዶላር
- ደረጃ ሁለት: ከ$250,000 እስከ $1,000,000 ዶላር

- ደረጃ ሶስት: ከ $1,000,000. ዶላር በላይ

በዚህ አዲስ መዋቅር ቀደም ሲል ለነበረው መግለጫ እና 'ላልተገርለጸ መዋቅር' ይተካል።

በህጋዊ የተዋሀዱ ማሕበራት አዲሱን መዋቅር መረዳት ሲኖርባቸው ታዲያ ይህ በሪፖርት ማድረግ ግዴታ ላይ ችግር ስለሚፈጥር እነሱ በየትኛው ደረጃ ላይ እንዳሉ ማጣራት አለባቸው። ለዝርዝር ሁኔታ በድረገጽ፤ consumer.vic.gov.au/associations መጎብኘት።

## ለፋይናሻል ጽሁፍ መግለጫ ማቅረቢያ አዲስ ቅርጽ ይዘት

በባጀት ዓመት ማለቂያ ቀን ወይም ከህዳር/ November 1 ቀን 2012 ዓ.ም በኋላ በቪክቶሪያ ሸማች ተጠቃሚ ጉዳይ ቢሮ በኩል ለዓመታዊ ጽሁፍ መግለጫ አዲስ ቅጽ ለማሕበራት ይልካል።

ከፋይናሻል ባጀት ዓመት ማለቂያ ቀን ማለት ሰኔ/June 30 ቀን 2013 ዓ.ም በፊት ማሕበራት በዚህ አዲስ ቅጽ ወይም በድሮ 'የመግለጫ/የማገልጽ' ቅጽ አድርጎ ዓመታዊ የፋይናሻል ጽሁፍ መግለጫ ለማስገባት ምርጫ ይኖራቸዋል። ለዝርዝር ሁኔታ የሚቀጥለውን ገጽ ይመልከቱ።

ዓመታዊ ጽሁፍ መግለጫን ለቪክቶሪያ ሸማች ጉዳይ ቢሮ ማስገባት የጸሀፊው (የቀድሞ ህዝባዊ ባለሥልጣን) ሃላፊነት ነው።

የማሕበሩ ዓመታዊ ፋይናሻል ቀን ከማለቁ በፊት የጽሁፍ መግለጫ ቅጹን ከመላክ ፋንታ፤ በአሁን ጊዜ የቪክቶሪያ ሸማች ጉዳይ ቢሮ **ከአንድ ወር በኋላ** ይልካል። የዓመታዊ ፋይናሻል ቀን ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ማሕበሩ አጠቃላይ ዓመታዊ ስብሰባ ለማካሄድና ዓመታዊ ጽሁፍ መግለጫ ለማቅረብ **የአምስት ወራት ጊዜ** ይኖረዋል።

ስለ ዓመታዊ ጽሁፍ መግለጫ ዝግጅት የበለጠ መረጃ ለማግኘት **ዓመታዊ ተከታታይና የፋይናሻል ሪፖርት (Annual cycle and financial reporting)** የሚለውን እውነታ ጽሁፍ ወረቀት ማየት።

## ጽሁፋዊ መግለጫን ለማቅረብ ምርጫዎች

በድሮ አንቀጽ ህግ መሰረት የተቋቋመ ህጋዊ ማሕበር የፋይናሻል ጽሁፍ መግለጫን በድሮው አንቀጽ ህግ መሰረት ለማዘጋጀትና ማስገባት ሲችል ነገር ግን ከሰኔ/June 30 ቀን 2013 ዓ.ም በፊት ላለ የበጀት ዓመት ማለቂያ ቀን ብቻ ነው።

ለምሳሌ፡ አንድ ማሕበር ከጥር/January 1 ቀን 2012 እስከ ታህሳስ/ December 31 ቀን 2012 ዓ.ም ላለ የፋይናሻል ጽሁፍ መግለጫ ለማቅረብ በአዲሱ ደረጃ አሰራር ወይም በድሮው 'የገላጭ/የማይገልጽ' አሰራር ዘዴ ለማቅረብ መምረጥ ይቻላል። በአዲሱ የደረጃ አሰራር ዘዴ የአንድ ማሕበር የበጀት ዓመት ማለቂያ ቀን ወይም ከሰኔ/June 30 ቀን 2013 ዓ.ም በኋላ ያላቸው የፋይናሻል ጽሁፍ መግለጫ መግባት አለበት።

አንድ ማሕበር የፋይናሻል ጽሁፍ መግለጫ 'የገላጭ/የማይገልጽ' አሰራር ዘዴን ተጠቅሞ ካስገባ ታዲያ ጸሀፊው የማስገቢያ ቅጽ ለማግኘት የቪክቶሪያ ሸማች ጉዳይ ቢሮን ማነጋገር ሲገባው፤ ይህም ማሕበሩ ለ2012-2013 ዓ.ም ዓመታዊ ሪፖርት የሚቀርበው በገላጭ ወይም በማይገልጽ ሪፖርት ተመርኩዞ ነው።

© State Government of Victoria (Consumer Affairs Victoria) 2014 

Consumer Affairs Victoria

## በመካሄድ ላይ ስላለ ሂደት

ማሕበሩ በድሮው አንቀጽ ህግ መሰረት ላቀረበው ማንኛውም ማመልከቻ ከአዲሱ አንቀጽ ህግ መጀመር በፊት ከተጠናቀቀ ታዲያ በአዲሱ አንቀጽ ህግ የማጣጠሚያ ማቅረቢያ መሰረት እንደወጡ ተደርጎ ግምት ውስጥ ይገባል።

በድሮ የአንቀጽ ህግ መሰረት ለሚገባ አብዛኛው ማመልከቻ ያለ ተጨማሪ መረጃ ጥያቄ የቪክቶሪያ ሸማች ጉዳይ ቢሮ ለማካሄድ ይችላል። ይሁን እንጂ ተጨማሪ ማብራሪያ ስንፈልግ ከማሕበሩ ምክር እንጠይቃለን።

በድሮ አንቀጽ ህግ መሰረት ለተደረገ ማንኛውም መፍትሄ፣ ቀጠሮ ወይም ማስታወቂያ በአዲሱ አንቀጽ ህግ መሰረት ተቀባይነት ይኖረዋል።

በድሮ አንቀጽ ህግ መሰረት በቪክቶሪያ ሸማች ጉዳይ ቢሮ የሚወሰድ እርምጃ በአዲሱ አንቀጽ ህግ መሰረት እንደተካሄደ ተደርጎ ይወሰዳል።

## የበለጠ መረጃ ከተፈለገስ?

### የቪክቶሪያ ሸማች ጉዳይ ቢሮ

የቪክቶሪያ ሸማች ጉዳይ ቢሮ በቪክቶሪያ ውስጥ ያሉትን ህጋዊ ማሕበራትን መመዝገብና መቆጣጠር እንዲሁም በህጋዊ ለተዋሀዱት ማሕበራት ህግን ያስተዳድራል።
ድረገጽ:consumer.vic.gov.au/associations

ተለፎን: 1300 55 81 81

### ፒልቾኮነቾት/Justice Connect

ፒልቾኮነክት/Justice Connect ተጽእኖ የሌለበት፣ ለትርፍ ያልቆመ ድርጅት ሲሆን ይህም ለየት ያለ ህጋዊ አገልግሎትን ማቅረብና ለማህበረሰባት ቡድኖች ምክርን ይለግሳል።

ድረገጽ: justiceconnect.org.au

ተለፎን: 03 8636 4400

State Government Victoria | Department of Justice